# <u>የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ለማዛወር ስለተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ የቀረበ አጭር ማብራሪያ</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ ቁጥር 146 በሥራ ላይ ከዋለ ሃያ ዓመታት አልፎታል፡፡ ይህ አዋጅ በተጠቀሱት ዓመታት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል በማዛወር ረገድ መሠረት የጣለና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል መዛወር የራሱን አስተዋጽዎ ያበረከተ ቢሆንም ሀገሪቱ ከምትከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር በተለይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለፕራይቬታይዜሽን ካለቸው ዝግጁነት፣በግል ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ ከሚኖራቸው ተወዳዳሪነት፣ የፕራይቬታይዜሽን አስፈጻሚ አካላት ከሚኖራቸው ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲሁም የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ግልጽና ታአማኒነት ያለው ከማድረግ አኳያ የህጉ መሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም መሠረት አሁን በሥራ ላይ ያለውን አዋጅ ቁጥር 146/1991ን የሚተካ 20 አንቀጾች ያሉት ረቂቅ አዋጅ የተዘጋጀ ሲሆን ማሻሻያ የተደረገባቸው ዋና ዋና ድንጋጌዎችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 1. <u>የፕራይቬታይዜሽን ትርጓሜ</u>

1) በሥራ ላይ ባለው አዋጅ ለፕራይቬታይዜሽን የተሰጠው ትርጓሜ የልማት ድርጅትን ወይም የልማት ድርጅትን የተወሰነ ክፍል ወይም ንብረት ወይም አክሲዮኖች ከማስተላፍ በተጨማሪ የመንግሥት መዋጮ ማድረግን እንዲሁም የልማት ደርጅትን ማኔጅመንት ወደ ግል ማስተላለፍን ያካተተ ነው፡፡ በረቂቁ አዋጅ የልማት ድርጅት ወደ ግል የማስተላለፊያውን መንገድ ንብረትን ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል በመሸጥ እንዲወሰን በማድረግ የልማት ድርጅትን ወይም የልማት ድርጅትን የተወሰነ ክፍል ማስተላፍ፣ የመንግሥት መዋጮ ማድረግ እንዲሁም የልማት ደርጅትን ማኔጅመንት ወደ ግል ማዛወር እንዳያካትት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በረቂቁ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (1) ፕራይቬታይዜሽን “የልማት ድርጅትን ንብረት ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል ለግል ዘርፉ በሽያጭ የማስተላፍ ውጤት የሚያስከትል ግብይት ነው” በሚል ተተርጉሟል፡፡

## 2. የፕራይቬታይዜሽን ዓላማ

የፕራይቬታይዜሽን ዓላማዎች ተብለው በረቂቁ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩት በሥራ ላይ ካለው ሕግ የሚለየው የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ውጤታማነት ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ የቴክኒክ ሙያንና ክህሎትን መጋበዝ እና የካፒታል አቅርቦትን ማሻሻል ቀዳሚ ዓላማ ሆኖ መካተቱ ነው፡፡

## 3. ስለቅድመ ፕራይቬታይዜሽን

በሥራ ላይ ባለው ሕግ ስለቅድመ ፕራይቬታይዜሽን የሚደነግገው አንቀጽ ወደ ግል የሚዛወሩ የልማት ድርጅቶች ዝርዝር በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን እንደሚወሰንና የደርጅቱ ማኔጅመንት ከኤጀንሲው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ውሳኔ የተሰጠበትን የልማት ድርጅት ለፕራይቬታይዜሽን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ሁሉ የመውሰድ ግዴታ እንዳለበት በጥቅሉ የሚደነግግ ነው፡፡

በሥራ ላይ ካለው በተለየ ሁኔታ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 4 ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች ተቋማት ማለትም የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ ወደ ግል የሚዛወር የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ እያንዳንዳቸው የሚኖራቸው ኃላፊነቶች በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት፤

- የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚኒስቴሩን እና የተቆጣጣሪውን ባለሥልጣን የውሳኔ ሃሣብ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል መዞር ያለበትን የልማት ድርጅት እንደሚወስን፤
- የገንዘብ ሚኒስቴር
    - ማናቸውንም የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች እንደሚያከናውን፣ ከሚመለከተው የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሂደት መቼ መጀመር እንዳለበትና የትኞቹ ሥራዎችም መካተት እንዳለባቸው እንደሚወስን፡፡
    - ከመንግሥት የልማት ድርጅቱ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመካከር የእያንዳንዱን ሽያጭ አመላካች የሽያጭ ዋጋ (ወይም መነሻና መድረሻ ዋጋ) እና ወደ ግል የሚዛወረውን የአክሲዮን መጠንን (የድርጅቱን መጠንን) እንደሚወስን፤

  - የመንግሥት የልማት ድርጅት ዋጋ ግምትን፣ እንደገና የማዋቀር ጥረቶች ውጤቶችን፣ ወቅታዊው የገበያ ሁኔታዎችን እና ድርጅቱ ኢንቬስተሮችን መሳብ የመቻሉን ዕድል ከግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ለመዛወር ያለውን ዝግጁነት እንደሚወስን፤
- ወደ ግል የሚዛወር የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ መረጃ መስጠትን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅትን ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽንና ለፕራይቬታይዜሽን ማዘጋጀትን፣ የልማት ድርጅት ንብረት ዋጋ እያሽቀለቆለ አለመሄዱንና ለብክነት አለመዳረጉን ማረጋገጥን፣ በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ወቅትና በፕራይቬታይዜሽን ደረጃ ማናቸውም አዲስ ኢንቬስትመንት ከማድረግ መቆጠብን በተመለከተ የሚኖሩበት ግዴታዎች፤

በግልጽ ተደንግጓል፡፡

## 4. ከፕራይቬታይዜሽን በፊት የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንደገና ስለማዋቀር

ከፕራይቬታይዜሽን በፊት የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንደገና ማዋቀርን በተመለከተ በሥራ ላይ ባለው ሕግ የተደነገገ ነገር የለም፡፡ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 5 ግን አንድ የልማት ድርጅት ተፈላጊነቱ እንዲጨምርና ዋጋው እንዲያድግ በሚያስችለው ቁመና ላይ እንዲገኝ ሚኒስቴሩ ከኤጀንሲው እና ከኤጀንሲው ውጭ ከሆነ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት ፤

- የልማት ድርጅቱ ወደ ግል ከመዛወሩ በፊት ተገቢው የካፒታል አደረጃጀቶች፣ የንግድ ስትራተጂ፣ የኮርፖሬት አስተዳዳር መዋቅሮች እና የሪፖርት አቀራረብና የመረጃ አገላለጽ ልምዶች ያለው መሆኑን የመገምገም፤ ጉድለት በሚኖርበትም ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ፤
- ከፕራይቬታይዜሽን በኋላ ተገቢ ያልሆነ የውድድር ባህርያት፣ የገበያ ልምዶች እና መጠኑ ያለፈ የገበያ የበላይነት እንዳይከሰት ከወዲሁ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ፤

ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑም በክትትል የደረሰባቸውን ማናቸውንም የኦፕሬሽን ግምገማዎችንና ተዛማጅ መረጃዎችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ እንደሚጠበቅበት ተመልክቷል፡፡

## 5. የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ስለመለወለጥ

የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ስለመለወለጥ የሚደነግገው አንቀጽ በስራ ላይ ካለው ሕግ የሚለየው በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 6 ሚኒስቴሩ የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክስዮን ማኅበርነት በሚለውጥበት ጊዜ ለአክሲዮን ማኅበሩ የሚተላለፉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ሀብትና ዕዳዎች እንዲሁም ንብረቶቹ እንደገና ከተገመቱ በኋላ ካፒታሉን መወሰንና ማሳደግን በተመለከተ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 69 (1) እና (2) የንግድ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ በተመለከተ የተደነገገው ተፈጻሚ እንዳይሆንባቸው መደንገጉ ነው፡፡

## 6. ስለፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸም

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 8 ከፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ኤጀንሲው እና ሚኒስቴሩ የሚኖራቸው ሥልጣንና ተግባራት በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አንቀጽ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአክሲዮን መተላለፍን የማጽደቅን እንዲሁም መንግሥት የሕዝብ ጥቅምን አያስጠብቅም ብሎ ባመነበት በማናቸውም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምጽ የመሻር መብት የሚያጎናጽፍ ወርቃማ አክሲዮን አጠቃቀምን፣ መዋቅርንና አተገባበርን የማጽቅ ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡፡ ኤጀንሲውም የሽያጭ ሥነ ሥርዐቶችና መስፈርቶች ማዘጋጀትን፣ ባለሙያዎች መቅጠርንና የሽያጭ ዋጋን መወሰን፣ ሽያጭን ማመቻቸትና ክትትል ማድረግን ጨምሮ ዝርዝር ተግባራት ተሰጥተውታል፡፡

## 7. <u>ስለፕራይቬታይዜሽን ስልቶች</u>

በሥራ ባለው ሕግ ኤጀንሲው አግባብነት ያላቸው የተለያዩ የፕራይቬታይዚሽን ስልቶችን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚቻልበትን ዝርዝር መመሪያ እንደሚያጠናና አስፀድቆ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ብቻ ነው የተገለጸው በረቂቁ አንቀጽ 9 ግን የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች አተገባበር በግልጽነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ እና ግቡም ለመንግሥት ተስማሚ የሆኑ ስምምነቶች ላይ መድረስ እንደሆነ በመደንገግ ስልቶቹን በዝርዝር አመላክቷል፡፡

## 8. ድህረ ፕራይቬታይዜሽን የኢንቬስትመንት ታሳቢዎች እና ግምገማዎች

በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትል የሚደረገው አሸናፊው ባቀረበው ፕላን መሠረት ነው፡፡ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 10 ግን የድኅረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትልና ግምገማ የሚካሄደው በሽያጭ ውሉ በተመለከተው መሆኑንና ገዢውም በተደረሰው ስምምነት መሠረት ማናቸውንም ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ኢንቬስትመንት

የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 11ኤጀንሲው የፕራይቬታይዜሽን ክንውኑን በተመለከተ ግምገማ የሚያካሂድ ገለልተኛ ባለሙያ በመሾም በግኝቶቹ ላይ ዓመታዊ ሪፖርት ማውጣት እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡

## 9. ስለታክስ

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 14 ታክስ የሚያርፍባቸውን ገቢዎች የሚመለከቱት ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ባለው ሕግ የሌሉ ናቸው፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት ታክስ የሚያርፍባቸውን ገቢዎች መወሰንን በተመለከተ የንብረት የእርጅና ቅናሽ ስሌት በአዋጁ አንቀጽ 7 መሠረት አክሲዮንን ወደ ግል ለማዛወር በገለልተኛ ባለሙያ በተገመተው ዋጋ ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን ሆኖም ግን የጨረታው ዋጋ አነስተኛ ከሆነ ታክሱ ገዢው በከፈለው ትክክለኛ ገንዘብ ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡

## 10. የፕራይቬታይዜሽን የተገኘ ገንዘብን ስለመጠቀም

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15 ከፕራይቬታይዜሽን ከተገኘ ገንዘብ ላይ ለክንውኑ የተደረገው ወጪ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ ሚኒስቴሩ በሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት በረቂቅ አዋጁ ውስጥ የተካተቱ አንኳር ጉዳዮች ሲሆኑ ዝርዝር ድንጋጌዎች የያዘው ረቂቅ አዋጁ ከዚህ ማብራሪያ ጋር አባሪ ሆኖ ቀርቧል፡፡